
# ቹ ቶማስ

# “ገነት በጣም እውነታ ነው”

## ከቪዲዮው የተወሰደ በጽሁፍ የቀረበ ማስረጃ




www.divinerevelations.info/Amharic

ማስታወሻ:- የመጽሐፉ ርዕስ በእንግሊዝኛው “HEAVEN IS SO REAL!” የሚል ነው።

**--------አቅራቢው እየተናገረ:---------**

በ 1992፣ ቹ ቶማስ የምትባል አንዲት ኮሪያዊ አሜሪካዊት፣ ዳግም የተወለደች ክርስቲያን ሆነች። ይህንን ታሪክ ልዩ የሚያደርገው ነገር፣ ከተለወጠች ከሁለት አመት በኋላ፣ ቹ በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ተጎበኘች። እሷ ወደ ገነት በተደጋጋሚ ታጅባ ብዙ ጊዜ ተወስዳለች እናም ሁለት ጊዜ ሲኦልን እንድታይ ተደርጋለች።

ቹ ቶማስ ስላጋጠማት (ስለ ራሷ ገጠመኞች) መጽሐፍ ጽፋለች፤ መጽሃፉ “ገነት በጣም እውነታ ነው” ይባላል፤ የታተመውም በ ኦክቶበር 2003 ነው።

በታተመ በአንድ ዓመት ውስጥ፣ ይህ መጽሐፍ በአለምአቀፍ ደረጃ ምርጥ የተሸጠ ተብሏል፤ በተጨማሪም በሰሜን አሜሪካ ግርማ ሞገስ ካላቸው አስር የክርስቲያን መጻሕፍት መሃል ተመድቧል።

እንዴት ነው አንዲት ቀላል የቤት እመቤት፣ የተወሰነ እንግሊዝኛ የምትናገር፣ መጽሐፍ ለማሳተም ሃላፊነት ተቀብላ ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን፣ በታተመ በአመት ውስጥ፣ አለም አቀፋዊ ምርጥ ሽያጭ ያካሄደ መጽሐፍ ሊሆን የቻለው ? ግን ምናልባትም ከሁሉም የላቀ ጠቃሚ ጥያቄ የሚሆነው ለምን እነዚህ ራእዮች አሁን።

“ገነት በጣም እውነታ ነው” እናም ይህ የ ቹ ቶማስ ታሪክ ነው።

**--------ቼ ቶማስ እየተናገረች:---------**

“መልካም. . .

ሰማያዊ አባት ሆይ፣ እመሰክር ዘንድ ስለፈቀድክልኝ አመሰግንሃለሁ። ሀሌሉያ። ከ1992 ጀምሮ ክርስቲያን ሆንኩኝ እናም ቤተ ክርስቲያን ለተወሰኑ ጊዜያት ከሄድኩኝ በኋላ ከኢየሱስ ጋር በጣም በፍቅር ተሳሰርሁ (በጣም አፈቀርኩት) እናም በቀሪው ህይወቴ በሙሉ ሁሉንም ማንነቴን (ሁሉንም የማንነቴን ቦታ) ለእርሱ ልሰጠው ፈለግሁ . . . ስለዚህ . . .

እና በደምብ አብራርቼ ‘ገነት በጣም እውነታ ነው’ ስለተባለው መጽሃፍ መናገር እፈልጋለሁ። ጌታ ኢየሱስ ራሱ ወደ ገነት አስራ ሰባት ጊዜያት በተቀየረው አካሌ ወስዶኛል፣ ማለትም የ15 እና የ 16 ዓመት ልጅ እያለሁ ያለኝን አካል ይመስላል። ከዚህ በፊት ግን፣ እርሱ ሁሉንም ነገር ተራ በተራ አዘጋጅቷል። በ1994 ሁሉንም አካሌን (ሰውነቴን) በቅዱስ እሳት አጥምቆኛል፣ ቀጥሎም ከአንድ ወር በኋላ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአምልኮ አገልግሎት ጊዜ ራሱን ገልጦ አሳየኝ። ቀጥሎም በ1995፣ በእሁድ ፋሲካ፣ እርሱ በሚንቀጠቀጥ አካል ቀባኝ እናም ከዛ ቀን ጀምሮ፣ አካሌ በቤተ ክርስቲያን ውስጥና በጸሎት ሰአቴ ጊዜ ይንቀጠቀጣል። ተመለከታችሁ፣ አሁን አካሌ ወደ ኋላና ወደ ፊት እየተንቀሳቀሰ ነው፣ ይህንን ካላደረግሁ ሆዴ ይወጣጠራል የሚፈነዳ ነው የሚመስለው፤ ለዛ ነው ወደ ኋላና ወደ ፊት የምንቀሳቀሰው። ስለዚህ እባካችሁ በአካሌ ላይ ሌላ የተሳሳተ ነገር እንዳታስቡ። ያን መንፈስ ቅዱስ ነው እየሰራ ያለው ምክንያቱም ስለ ኢየሱስ እየመሰከርኩ ስለሆነ፣ ስለዛ ነው። እናም ቀጥሎ፣ ከዚህ በኋላ፣ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ፣ በአዲስ ልሳኖች፣ በሰማያዊ (ገነታዊ) መዝሙሮች፣ በቅዱስ ሳቅ አጠመቀኝ እናም ለሶስት ሰዓታት ያህል ከላይ በነገርኋችሁ ተሞልቼ (ተቀብቼ) መሬት ላይ ነበርሁ፣ በጣም ሃያል ስለነበር መነሳት እንኳ አልቻልኩም። ከዛ ቀጥሎ፣ ከተወሰኑ ወራት በኋላ፣ ካህን ላሪ ራንዶልፍ፣ እግዚአብሔር እኔን ልዩ በሆነ መልኩ ሊጠቀምብኝ እንደሆነ በኔ ላይ ትንቢት ተናገረ፤ ይህንንም ነገረኝ። እናም ይሄ ሁሉ ትንቢት በትክክል መጥቷል፣ አንድ ሺህ እጥፍ በበለጠ መልኩ። እናም ከዚህ በመቀጠል፣ ጃንዋሪ 1996፣ ጌታ ኢየሱስ እያየሁት መጥቶ እየጎበኘኝ ነበር። እርሱ እንዴት እንደሚጠቀምብኝ ፣ እናም ሁሉም ነገሮች፣ የእርሱ እቅዶች፣ ስለ እቅዶቹ ሊነግረኝ ለ አስር ጊዜያት ያህል መጥቶ ነበር፤ እነዚህም ነገሮች ሁሉ በመጽሃፉ ተካተዋል። ወደ ገነት እንደሚወስደኝ ግን አልነገረኝም ነበር። ስለዚህ፣ ከ አስር ጊዜያት በኋላ በ ፌብሩዋሪ 1996፣ በተቀየረው አካሌ ወደ ገነት ይወስደኝ ጀመር፣ ይህ አካሌ የእርሱን መንፈሳዊ አካል ይመስል ነበር። በእያንዳንዱ ጊዜ እኔን ወደ ገነት ከመውሰዱ በፊት፣ በዚህ ምድር ላይ ወዳለ ባህር ዳርቻ ይወስደኝ ነበር። ለመጀመርያ ጊዜ እርሱ እኔን ወደ ገነት ከመውሰዱ በፊት፣ በባህሩ ዳርቻ በአንድ ጎን ወሰደኝና እንደ መስታወት ንፁህ የሆነ ትንሽ የውሃ አካል አሳየኝ በመቀጠልም የሚያብረቀርቅ ትልቅ መሿለኪያ አሳየኝ። ስለዚህ ከዛ በኋላ ወደ ገነት ወሰደኝ። ”

**--------አቅራቢው እየተናገረ:---------**

“በመሿለኪያው ውስጥ ካለፈች በኋላ፣ ቼ እንዲህ ብላ ጻፈች :

*ከተራራ ጫፍ ላይ እየወረደ በመጣው መንገድ ላይ ጌታና እኔ አብረን ተጓዝን። በመጨረሻም ከትልቅ ነጭ ህንፃ ፊት ከነበረ ከግዙፍ በር ጋር ደርሰን ቆምን። ከገባን በኋላ፣ እጅግ ትልቅ ወደ ሆነ ክፍል ወደሚያመራ ረጅም ኮሪደር ላይ ተጓዝን። ከዛም ወደ ክፍሉ ገባን። ወደታች ስመለከት ምድር ላይ ባለው ባህር ዳርቻ ላይ እያለሁ ከለበስኩት ልብስ የተለየ ልብስ እንደለበስኩ ለመጀመርያ ጊዜ አስተዋልኩ፣ በመቀጠልም በራሴ ላይ ከበድ ያለ ነገር እንዳለ ተሰማኝ። እጄን አንስቼ ለማረጋገጥ ስሞክር እጅግ የሚያምር ዘውድ እኔ ሳላውቀው እዛ ጋር እንዳለ አስተዋልኩ። ከዛ ቀጥታ ወደ ጌታ ተመለከትኩ። እርሱ በዙፋን ላይ ተቀምጦ፣ እጅግ የሚያበራ ብሩህ ደማቅ ልብስ ለብሶና ወርቃማ ዘውድ ደፍቶ ነበር። ሌሎችም ከእኔ ጋር እዛ ነበሩ፣ በመሬት ላይ ተንበርክከውና በፊቱ ሰግደው ነበር። የቤቱ ግድግዳ ከሚያበሩና ከሚያንፀባርቁ ድንጋዮች የተሰራ ነው። የተለያዩ ቀለም ያላቸው አለቶች ቤቱን ሞቃትና ደስተኛ እንዲሁም ምስጢራው እንዲመስል (እንዲሆን) የራሳቸው የሆነ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ከዛም በፍጥነት፣ ወደ በፊቱ ተራራ ከዛም ወደ ትልቁ ነጭ ህንፃ ተወሰድኩ ከዛም ራሴን እዚህ ምድር ላይ ያለው ባህር ዳርቻ ላይ አገኘሁት።”*

**--------ቼ ቶማስ እየተናገረች:---------**

*የመጀመርያው ቀን የራሱን የዙፋን ክፍል ብቻ ነው ያሳየኝ። ከዛ በኋላ ከገነት ተመልሰን ምድር ላይ ባለው የባህር ዳርቻ አሸዋ ላይ ቁጭ አልን። ከዛም እርሱ(የናዝሬቱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ) መናገር ጀመረ፣ እንዲህም አለ **“አሁን ሄደን የነበረው ወደ ገነት መንግስት (መንግስተ ገነት) ነው። ወደዛ የሚመጡት ታዛዥና ንፁህ ልቡና ያላቸው ብቻ ናቸው፤”** እናም እንዲህ አለ **“ወንጌልን መስበክ በጣም ጠቃሚ ነው፤”** እና ለተወሰነ ጊዜ ጠበቀና እንዲህ አለ **“አስራት የማያወጡ(የማይሰጡ) የማይታዘዙ ክርስቲያኖች ናቸው።”** ያ በመጀመሪያው ጉዞ ለመጨረሻ ጊዜ የተናገራቸው ቃላቶቹ ናቸው።*

**--------አቅራቢው እየተናገረ:---------**

ቹ ለ16 ተጨማሪ ጊዜያት ገነትን ለመጎብኘት ሄዳለች፣ በእያንዳንዱ ጉብኝቶቿ ይህንን ጽፋለች:

*"በተለወጠው አካሌ፣ ከጌታ ጋር አብሬ በባህር ዳርቻው ላይ ተጉዣለሁ፣ ከዛም ወደ ገነት ይመራኝ (ያጅበኝ) ነበር። ባሸበረቁና በሚያምሩ በሮች እንገባና ልብሳችንን ለመቀየር ወደ ነጩ ህንጻ እንሄዳለን። ከቀየርን በኋላ በወርቃማው ድልድይ ላይ እንሄዳለን። ለእኔ ሁሉም ነገር እንደ ተፈጥሯዊ(የተላመድኩት ነገር) ይሆንልኝ ጀመር። እያንዳንዱ አማኝ፣ ወደ ገነት በሚሄድበት(በምትሄድበት) ሰዓት በተመሳሳይ ሥርዓት ውስጥ እንደሚያልፍ እርግጠኛ ነኝ።"*

**--------ቹ ቶማስ እየተናገረች:---------**

ከዛ በኋላ፣ ጌታ ለ16 ተጨማሪ ጊዜያት ወደ ገነት ወሰደኝ። በእያንዳንዱ ጊዜ እርሱ እዛ ሲወስደኝ የተለያዩ ነገሮችን አሳይቶኛል። ለየት ያሉ ነገሮችን ሲያሳየኝ፣ ሁልጊዜ፣ ***"ይህንን ለልጆቼ ነው ያዘጋጀሁት"*** ይለኛል፤ ***"ምን እንደሚወዱ አውቃለሁ።"*** የባህር ዳርቻ ሲያሳየኝ፣ ***"ይህ የባህር ዳርቻ ምን ያህል እንደሚያምር አየሽ ለጄ፣ ልጆቼ ይሄንን የባህር ዳርቻ እንደሚወዱት አውቃለሁ"***፤ አሳ ለማጥመድም ሲወስደኝ፣ ***"ልጆቼ አሳ ማጥመድ እንደሚወዱ አውቃለሁ፣ ለዛም ነው እጅግ ብዙ የሚወዷቸውን ነገሮች ያዘጋጀሁት"***። ገነት ከዚህ ምድር (መሬት) አንድ ሺህ እጥፍ እንደሚያምር አስተውያለሁ፤ ብዙ ነገሮች ግን መሬት ካሉ ነገሮች ጋር ይመሳሰላል፣ መንገዶች፣ ህንፃዎች፣ ዛፎች፣ ቁጥቋጦዎች፣ አለቶች፣ አበቦች፣ ከመንግስቱ ውጪ ደግሞ ኮረኮንች(ልሙጥ ያልሆኑ) መንገዶች፤ እጅግ ብዙ ነገሮች እዛ አሉ፣ ነገር ግን መሬት ካሉት ነገሮች አንድ ሺህ እጥፍ ያምራሉ፣ በጣም ያምራሉ። የገነት ውበት ሊገለፁት የማይቻል ነው፣ ምን ያህል እንደሚያምሩ ሁላ መግለጽ አልችልም፣ በጣም ያምራሉ። ከዛም፣ ኢየሱስ እያንዳንዳችንን ምን ያህል እንደሚያፈቅረን ተገነዘብኩ። እርሱ እንዲህ እያለ በዚህ መንገድ ያናግረኝ ነበር ***"ምን ያህል ልጆቼን እንደማፈቅራቸው ተመለከትሽ፣ ይህንን ሁሉ ያደረግሁት ለልጆቼ ነው"***፣ ታውቃላችሁ። ለልጆቹ ምን እንዳዘጋጀ ያሳየኝ ዘንድ ነው እዛ የወሰደኝ። ስለዚህ እያንዳንዳችሁና ሁላችሁም በገነት ምን እየጠበቀን እንደሆነ እወቁ። እርሱ ከመምጣቱ በፊት፣ ሁሉም ክርስቲያኖች ይህንን ያውቁ ዘንድና ጉጉ ሆነው እዛ እንዲሄዱ ይፈልጋል። ለዛ ነው ይህንን ያሳየኝ ምክንያት ይሄ እንደሆነ ያመንኩት። ሁሉንም ነገር አልነገረኝም፣ ታውቃላችሁ፣ በዝርዝር፤ የተወሰኑ ነገሮችን ነው ያሳየኝ፣ የተወሰኑ ቃላቶችን ብቻ፣ አስፈላጊ ቃላቶችን ብቻ ነው የነገረኝ። ያው እርሱ አፍቃሪ አምላክ (እግዚአብሔር) ነው። አመሰግንሃለሁ ጌታዬ።

**--------አቅራቢው እየተናገረ:---------**

ገነትን ከመጎብኘቷ ጎን ለጎን፣ ቹ ሁለት ጊዜ ሲኦልን አይታለች።

በሲኦል ያየችውን ራዕይ እንዲህ ትገልፀዋለች : *ከጥልቁ የሲኦል ጉድጓድ ውስጥ ለመተንፈስ የሚያስቸግር መጥፎ ሽታና የጨለመ ጥቁር እንፋሎት ወደላየ ሲወጣ እመለከት ነበር። የእሳተ ገሞራ አናት ይመስል ነበር። ብዙ ሰዎችን የእሳት ነበልባል በሚያንገበግብ ሙቀት እያቃጠላቸው እጅግ በሚያሳዝን መልኩ እየጮሁና እያለቀሱ ተመለከትኩ፣ በእውነቱ የስቃያቸውን መጠን በእሳቱ እየነደዱ ከሚቃጠሉት ሰዎች በቀር ማን ሊያውቀው ይችላል።*

*ሰዎቹ ራቁታቸውን ነበሩ፣ ፀጉርም የላቸውም፣ በጣም ተጠጋግተው አጠገብ ላጠገብ ቆመው እንደ ትል ይጓዙ ነበር፣ የእሳቱ ነበልባልም ሰውነታቸውን እጅግ በሚያንገበግብ ሙቀት ያቃጥለው ነበር። አንዴ በሲኦል ጉድጓድ ውስጥ ለገቡት ሰዎች ማምለጫ መንገድ የላቸውም፣ ግድግዳዎቹ በጣም ጥልቅ ስለሁኑ ለመዝለል አይችሉም፣ በሁሉም ጫፎቻቸውና በጠርዞቻቸው ላይም በጣም የሚያቃጥሉ የእሳት ከሰሎች ያሉባቸው ናቸው።*

*የእሳት ነበልባሎቹ በድንገት ከሁሉም አቅጣጫ ዘለው ይወጣሉ። ሰዎቹም ወደሌላው አቅጣጫ ይሄዳሉ፤ ልክ ደህና ቦታ ላይ ነን ሲሉ፣ ሌላ እሳት ወደእነሱ ይመጣል። ለነዚህ በሃጢአት ለተጎዱና ለሞቱ ምንም እረፍት የላቸውም፤ በእሳት እየነደዱና እየተቃጠሉ ከሲኦል እሳትም ለማምለጥ እየለፉ ለዘለአለም አልቆላቸዋል። "እነዚህ ሰዎች ማናቸው ?" ብዬ* ጠየኩት ። ***"ልጄ፣ እነዚህ ሰዎች እኔን አያውቁኝም"***

**--------ቹ ቶማስ እየተናገረች:---------**

*በገነት ያሳየኝ ማንኛውም ነገር በጣም አስደናቂና ደስ የሚል ነው። ከዛ ቀጥሎ ግን ሲኦልን አሳየኝ። ወደ ሲኦል ወሰደኝ፣ ለመጀመርያ ጊዜ ያየሁት ሙሉ እሳት ነው ግን በጣም ጥልቅ፣ጭለማና መጨረሻ የሌለው ጥልቅ ቀዳዳ ነው። ሰዎች ያለምንም ፀጉርና ራቁታቸውን ነበሩ። እነሱ ምንም ፀጉር የላቸውም፣ ምንም የለበሱት ልብስም የላቸውም፣ ሙሉ ራቁት ሠውነት (አካል)። በጣም ተቀራርበው ቆመው ነበር። ከእሳቱ ለመራቅ ስለሚፈልጉ እርስ በርሳቸው ይገፋፉ ነበር።*

*በያንዳንዱ ጊዜ ሲንቀሳቀሱ እሳቱ ይከተላቸው ነበር፣ ወደኋለ ወደፊት፣ ወደኋለ ወደፊት፤ ሙሉ ቦታው እንዳለ እሳት ነበር፣ እኚህ ሰዎች በጣም ተቀራርበው ቆመው ነበር። በታላቅ ህመምና ስቃይ ያሉ ይመስላሉ፤ ልረዳቸው ስላልቻልኩ በጣም አለቅስ ነበር። ከዛም ለሁለተኛ ጊዜ ሲወስደኝ እነዛውኑ ሰዎች በድጋሚ አየኋቸው። ከዛም ድምፆች ሠማሁና ወደዛ ቦታ ተመለከትኩ፣ ብዙ የሩቅ ምስራቅ ሠዎችን ተመለከትኩ፤ አንዲት ሴት፣ እጇን እያውለበለበች (እያንቀሳቀሰች) በጣም ይሞቃል በጣም ይሞቃል ትል ነበር። ወደሷ ተመለከትኩ፣ አይኖቻችን ተገጣጠሙ። ያቺ እናቴ ናት፣ እናቴ እንደሆነች ሳገናዝብ ልቤ ወደቀ እናም ማልቀስ ጀመርኩ። እንደዚህ አይነት ህመም በጭራሽ ተሰምቶኝ አያውቅም፣ ህመም ብቻ። ታላቅ ህመም፣ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅሁም፣ በጣም ያቃጥላል በጣም ያቃጥላል ማለቷን ቀጠለች፣ ወደእኔም በእጇ ምልክት ትሰጠኝ ነበር። እንዳየሁት ከሆነ፣ ወደሷ ወርጄ እንድረዳት ፈልጋ ነበር። በድጋሜ ሌሎች ሰዎችን ተመለከትኩ፣ አባቴን፣ የእንጀራ እናቴን፣ ወጣቱን የአጎቴን ልጅ፣ በልጅነቱ ነበር የሞተው፤ እናም ሁለት አውቃቸው የነበሩ ጓደኞቼን። ኦህ፣ ያ በጣም የሚያሳምም ትውስታ ነው እናም ማልቀስ ማልቀስ ማልቀስ ቀጠልኩ፤ ከዛ ጌታ ኢየሱስ ይህንን ነገረኝ* ***"ልጄ፣ ይህንን አሳይሽ ዘንድ ጥሩ ምክንያት አለኝ፣ ግን አንቺ ከተጎዳሽው በላይ እኔ ተጎድቻለሁ"*** *። ኡም. . እናም ይህን ነገርኩት : ጌታሆይ፣ እናቴ፣ ወጣት እያለች ነበር የሞተችው፣ ለረጅም ጊዜ በጣም ታማ ነበር። መጥፎ ሰው ናት ብዬ አላስብም*። እርሱም እንዲህ አለ "***ምንም ያህል ሰዎች ጥሩ ቢሆኑ፣ እኔን የማያውቀኝ ማንም ሰው፣ ብቸኛው የሚሄዱበት ቦታ ያ ነው***።" *ነገር ግን በልቤ፣ በዚህ መንገድ እኔን ለመጉዳት ለምን ይህንን አሳየኸኝ። ስለዛ አሰብኩ፣ በጭራሽ ግን በሱ ላይ አልተናደድኩም። ፊቱን ላየው አልቻልኩም ነገር ግን ከእኔ ጋር እያለቀሰ እንደሆነ መናገር እችላለሁ። ያ ተሰምቶኛል። በጣም አዝኖ ነበር። ከዛ ጭንቅላቴን ነካኝ ቀጥሎም እጆቼን ይዞ ከዛ ቦታ ለመውጣት ጉዞ ጀመርን፣ በጉዞአችን ሙሉ እያለቀስኩ ነበር። በመጽሃፉ ውስጥ እያንዳንዱን ነገሮች አብራርቼ ገልጨዋለሁ። ስለዚህ፣ በመቀጠል፣ በቀጣይ ጉብኝት ሌላ በጣም አሳዛኝ ነገር አሳየኝ። በእናታቸው ማህፀን ሳሉ የወረዱ ህፃናት (ከመወለዳቸው በፊት እንዲሞቱ የተደረጉ ህፃናት)፤ በገነት አንድ ግዙፍ ህንፃ ወዳለበት ቦታ ወሰደኝ፣ ግምጃ ቤት (መጋዘን) ይመስል ነበር። ወደ ውስጥ ስገባ አየው የነበረው ሁሉ ህፃናትን ነው፣ ቀጫጭን፣ ራቁታቸውን የሆኑ ቀጫጭን ህፃናትን። እናም ጎን ለጎን ሆነው ተጋድመው ነበር። ኹም. . ማልቀስ ጀመርኩ። ጌታ ሆይ፣ ለምንድን ነው ብዙ ህፃናት ያሉት*። እርሱም እንዲህ አለ ***"እነዚህ የወረዱ ህፃናት ናቸው"*** *። ምን ልታደርጋቸው ነው ያሰብከው አልኩ። እርሱም* ***"እናቶቻቸው ከዳኑና ወደ ገነት ከመጡ፣ ልጆቻቸውን በድጋሜ ማግኘት ይችላሉ"*** አለ። *ያ ነው በቃ*

**--------አቅራቢው እየተናገረ:---------**

ወደ ገነት 17ኛ ጉዞዋ ላይ፣ ኢየሱስ ለ ቹ ይህ ወደገነት የምታደርገው የመጨረሻ ጉዞዋ እንደሚሆን ነግሯት ነበር። በዚህ ላይ እንዲህ ጽፋለች:

*"የእርሱ ቃላቶች በጥልቀት አወከኝ። በእርግጥም ልቤ ለጌታዬ ባለው ፍቅር ታመመ። ጌታዬም ተነሳ፣ እኔም ለእኛ የመሄጃ ሰዓት እንደሆነ አወቅሁ። ማልቀስ ቀጠልኩ፣ ልቤ ግን በአንድ እውቀት እርግጠኛ ሆነ፣ ያም ከጌታ ጋር ለዘለአለም አንድ ላይ እንደምሆንና በዚህ ምድርም ሁልጊዜ አብሮኝ እንደሚሆን። በመልበሻው ክፍል፣ የጌታ መልአክ አቀፈኝ። እጅግ ብዙ ፍቅር፣ መተሳሰብና መግባባት ሁሌም ባለበት ቦታ መሆን እጅግ በጣም የሚያስደስት ነው። ልብሴን እየቀየርኩ ሳለ፣ አብርሃምና መልአኩ ይሄ የመጨረሻው የገነት ጉብኝቴ መሆኑን እንዳወቁ ገመትሁ። ከልብስ መቀየርያው ክፍል ወጥቼ ስጓዝ፣ መልአኩ ተጨማሪ አንድ ጊዜ አቀፈኝ። ይህ መልአክ ፈዘዝ ያለ ቢጫ ፀጉር፣ እታች የደረሰ ነጭ ልብስ (ካባዎች)፣ ለስለስ ያለና የተረጋጋ ሞቃት ፊት አለው። ወደ ጌታ እየተራመድኩ ስሄድ መልአኩ ፈገግ ብሎ(በፈገግታ) አየኝ፡*

**--------ቹ ቶማስ እየተናገረች:---------**

*ጌታ ኢየሱስ ለ17ኛ ጊዜ ወደ ገነት ሲወስደኝ፣ ዳመናዎችን አሳየኝ፣ ያም በገነት የመጨረሻው ጉብኝቴ ነበር። ጌታ ኢየሱስ* እንዲህ ብሎ ነግሮኝ ነበር "***ይህ እዚህ የሆንሽበት የመጨረሻው ጊዜ ነው። የመጨረሻዋ ቀን እስክትመጣ ድረስ በድጋሜ እዚህ አላመጣሽም***።" *ይህን አስቀድሜ እንደማውቀው ተሰማኝ፣ ያ የመጨረሻው የጉብኝት ቀን ነው። እናም ያንን ቦታ መልቀቅ ስላልፈለግሁ ማልቀስ ጀመርሁ። የጌታን ክንድ ይዤ እንዲህ አልሁ "ጌታ ሆይ፣* እባክህ *እንድሄድ አታድርግ፣ መሄድ አልፈልግም ምክንያቱም በተደጋጋሚ* እዚህ *መምጣት እፈልጋለሁ።" በድጋሜ እዛ መሄድ አለመቻሌ ለእኔ እጅግ እጅግ የሚያሳዝን ነበረ፤ ምክንያቱም በእያንዳንዱ ጊዜ አብሬው ወደ ገነት ስሄድ፣ የሚያሳዝን ነገር አይቻለሁ፣ ነገር ግን ደስታና ሰላምን ልገልፀው አልችልም፤ እዛ ሳለሁ ያለኝን ደስታ(ሀሴት) ና ሰላምም እንዲሁ ልገልፀው አልችልም። ባዝንም እንኳ፣ አሁንም ደስታና ሰላም አለኝ። በጣም ብዙ ፍቅር፣ ለዛ ብዙ ቀናት አልቅሻለሁ።*

**--------አቅራቢው እየተናገረ:---------**

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ ዳግም ተመልሶ ስለሚመጣበት ቀን ይናገራል። በ1ኛ ተሰሎንቄ 4:16 እንዲህ ይነበባል "ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፣ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሳሉ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፣ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።" ይሄ ተነጥቆ ወደ ገነት መወሰድ (መነጠቅ ፣ማረግ) ይባላል።

**--------ቹ ቶማስ እየተናገረች:---------**

*ከሁሉም ነገር ገኋላ፣ ከተወሰኑ ሳምንታት በኋላ፣ ጌታ ኢየሱስ በዚህ ምድር ወዳለው የባህር ዳርቻ የኔን መንፈሳዊ አካልና የሱን አመጣ። እናም በተለመደው ቦታ ተቀመጥን፣ ለተወሰነ ጊዜ ካወራን በኋላ እርሱ የሚከተለውን ነገረኝ **"አንድ ነገር አሳይሻለሁ"** ያንን ባለበት ደቂቃ የራእይ ድምፅ ከእኔ ወጣ። ሁል ጊዜ የተለየ ነገር ሲያሳየኝ፣ ለየት ያለ ከውስጥ አካሌ (ከሆዴ) የሚወጣ የራእይ ድምፅ አገኛለሁ። በጣም የሚጮህና ይኼኛው የራእይ ድምፅ ረዘም ያለ ጊዜ የወሰደ ነበር። በመቀጠልም ድምፆችን (ጫጫታዎችን) እሰማ ነበር፣ እጅግ በጣም በጣም ከፍተኛ ጩኸቶችን፣ሙሉ አለም ሁሉ ወደዛ የመጣ ነው መስሎ የተሰማኝ፣ በጣም ከፍተኛ፣ አስከፊ (አሰቃቂ) ጩኸቶች። ከዛም ተመለከትኩ፣ ሙሉ አየሩ ነጭ ነበር። ነጭ ልብስ የለበሱ ሰዎች ሁሉም ቦታ ይበሩ ነበር፣ ወደላይ መወሰዳቸው ቀጥሎ ነበር፣ ወደላይ ይወሰዳሉ፣ ከዛም በድንገት ይጠፋሉ፣ ወደላይ ይወሰዳሉ፣ በአየር ይሞላል፣ በሰዎችም። ከዛም፣ ሰዎቹ ወደላይ እየተነጠቁ እየተወሰዱ እንደሆነ አወቅሁ። እየሳቅሁኝ፣ እያለቀስኩኝ፣ እየጮህኩኝ፣ በጣምም ተገርሜና ተደስቼ ነበር፤ በመቀጠልም የልጅ ልጄን አየኋት፣ አሁን አስር ወሯ ብቻ ነው፣ ምንም ፀጉርም የላትም፤ በድንገት ከቤት ውስጥ በመስኮት በኩል አርጋ ወደላይ በረረች። ነጭ ልብስ ለብሳና ፀጉሯም ወደ ትከሻዋ ደርሶ ነበር። እንዴት ደስተኛ ልሆን እንደምችል ማሰብ ትችላላችሁ። ከዛ በቀጣዩ ደቂቃ፣ ሌላኛዋን የልጅ ለጄን አየኋት፣ አራት ወሯ ብቻ ነበር፣ ምንም ፀጉር የላትም፣ ልክ እንደ ሌላኛይቷ የልጅ ልጄ እሷም ነጭ ልብስ አድርጋ በመስኮት በኩል ወደሰማይ በረረች፣ ይህ በሚሆንበት ሰዓት ፀጉሯ ትከሻዋ ላይ ደርሶ ነበር። እየጮህኩኝ፣ እያለቀስኩኝ፣ እየሳቅሁኝ፣ በጣምም ተገርሜና ተደስቼ ነበር፣ ከዚህ በፊት በጭራሽ የዚህን ያህል ተደስቼ አላውቅም፣ በጣም ተደስቼ ነበር፣ ሙሉ ቤቱ መስማት ይችል ነበር። ጥሩ ነገሩ ባለቤቴ ቤት ውስጥ አለመኖሩ ነው። ቤት ውስጥ ሆኖ ቢሆን ኖሮ፣ በርግጠኝነት እኔ ጋር አንድ ችግር እንዳለ አርጎ ያስብ ነበር። እናም ከዛ በመቀጠል እግዚአብሔር የተለያዩ ትዕይንቶችን አሳየኝ። ይሄኛው ትዕይንት እጅግ የሚያሳዝን ነው። አስከፊ ነበር*።

**--------አቅራቢው እየተናገረ:---------**

መጽሐፍ ቅዱስ፣ በተጨማሪ ከክርስቶስ ኢየሱስ ሙሽሮች መነጠቅ (መወሰድ) በኋላ ስለሚመጣው ስለታላቅ መከራ (ጭንቀት ፣ስቃይ) ይናገራል። በማቴዎስ 24:21-22 ኢየሱስ እንዲህ ብሏል "በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናል። እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ስጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ።" ይሄ ታላቁ መከራ በመባል ይታወቃል።

**--------ቹ ቶማስ እየተናገረች:---------**

*መልካም፣ ከዛ ቀጥሎ፣ ጌታ ኢየሱስ ሌላ ራእይ አሳየኝ። ይሄ ከጌታ ጋር ተነጥቀው ወደ ገነት ከመሄድ ቀርተው በዚሁ ምድር ለመከራው ዘመን ስለቀሩት ሰዎች ነው። ከነዛ ሰዎች መሃል ብዙ ክርስቲያኖች አብረው እንዳሉ አምናለሁ። ለዛ ነው ሲሮጡ የነበሩት፣ ትክክል አይደል? ክርስቲያኖች ባይሆኑ ኖሮ፣ አይሮጡም ነበር፣ ታውቃላችሁ አይደል። ነገር ግን ፖሊሶች ሁሉም ቦታ ነበሩ፣ ሰዎች ሁሉም ቦታ ነበሩ፣ ዝምብለው ይሮጡም ነበር፣ ፈርተው ነበር፣ የድንጋጤ ፊት ይታይባቸው ነበር፣ ወደ መኪናም ይሄዱ ነበር፣ ወደ ጀልባም ይሄዱ ነበር፣ ወደ ተራራም ይሮጡ ነበር፣ ወደ የት መሄድ እንዳለባቸው አያውቁም ነበር፣ አንድ ነገር የሚያሳድዳቸው ይመስሉ ነበር፣ ታውቃላችሁ አይደል ፣ በጭራቅ ወይም በሌላ ነገር የሚሳደዱ ይመስሉ ነበር፣ ያ በጣም የሚያስፈራና አስከፊ አስከፊ ትእይንት ነበር። ከዛ በኋላ ጌታ ኢየሱስ ይህንን ነገረኝ **"አሁን ያየሽው ነገር ያ ቀን ሲመጣ ከሚከሰተው ነገር ጋር ሲወዳደር እንደምንም ነው።"*** ከዛ ቀጥሎ ይሄንን ነገረኝ ***"ሁሉም ህዝቤ ይነጠቃል፣ ከዛም ሰይጣን ይህንን አለም ይቆጣጠራል እናም ሁሉም ሰዎች የሱን ቁጥር 666ን እንዲቀበሉ ይፈልጋል፣ እናም ምልክቱን አልቀበልም ያለ ማንም፣ ራሳቸውን ይቆረጣሉ።"** ስለዚህ የአውሬውን ምልክት 666ን ያልተቀበለ ማንኛውም፣ ልባቸውን ለኢየሱስ ሰጥተዋል፣ ከዘለአለም እስከዘለአለም ከእርሱ(ክርስቶስ ኢየሱስ) ጋር ለመሆን ፈልገዋል፣ የዮሐንስ ራእይ 20:4። እናም ቀጥሎ፣ ማንም ቢሆን የአውሬውን ምልክት 666ን የተቀበለ፣ ሁሉም ለዘለአለም እስከ ዘለአለም ወደ እሳት ባህር ይጣላሉ፣ ቀንና ሌሊትም በእሳቱ ይነዳሉ፣ ምንም እረፍት የላቸውም፣ የዮሐንስ ራእይ 14:11። ስለዚህ ሁሉም*

*ሰው ስለዚህ ነገር ማወቅ፣ ማስታወስና አንገቱን ለመቆረጥ መፈለግ አለበት፣ ቀላል መንገድ አይሆንም። አንገታቸውን ከመቆረጣቸው በፊት በጣም በአሰቃቂ ሁኔታ ይሰቃያሉ፣ ምክንያቱም፣ ሰይጣን በቀላሉ እንዲገደሉ አይፈቅድላቸውም። ስለዚህ ማንኛውም ይህንን መልዕክት የሰማ፣ እባካችሁ ከጌታችን ኢየሱስ ጋር የቀረበ ግንኙነት (የጠበቀ ወዳጅነት፣ዝምድና) ከሌላችሁ፣ እባካችሁ ስለ ደህነታችሁ የሆነ ነገር አድርጉ። በተጨማሪም፣ እዚህ ምድር ላይ ለመከራው ዘመን ከቀራችሁ፣ ምንም ያስከፍል ምን፣ በምንም አይነት መልኩ በምንም አይነት መልኩ የአውሬውን ምልክት 666 እንዳትቀበሉ። ለዘለአለም እስከዘለአለም በሲኦል በእሳት ከመንደድ ለተወሰነ ጊዜ ስቃይና መከራን መቀበል ይሻላል። እባካችሁ፣ እባካችሁ እያልኩት ያለውን ነገር ከልብ (በትኩረት) ተቀበሉት (ውሰዱት)*።

**--------አቅራቢው እየተናገረ:---------**

“ገነት በጣም እውነታ ነው” የሚለው መጽሐፍ፣ ወደተለያዩ አገር ቋንቋዎች እየተተረጎመና በአለም ሁሉ ዙሪያ እየተከፋፈለ ይገኛል። በተጨማሪም በቀጥታ (ኦንላይን) መግዛት የሚቻል፣ የዚህ መጽሃፍ ኤም ፒ ስሪ (MP3) ትርጉም አለ።

**--------ቹ ቶማስ እየተናገረች:---------**

*መልካም፣ መጽሐፉ ጥሩ እየሰራ ነው። እና ይሄ መጽሐፍ አለምአቀፋዊ ምርጥ የተሸጠ መጽሃፍ ነው። ጌታ ኢየሱስ፣ ዶክተር ዮንጊ ቾን ይህን መጽሐፍ ይተረጉመው ዘንድ መርጦታል። ለመተርጎም ሁለት ወር ወስዶበታል፣ አብዛኛውን ጊዜ ግን ስድስት ወይም ሰባት ወራት ይወስድ ነበር። ስለዚህ፣ መጽሐፉ የታተመ እለት፣ በኮሪያ በአንድ ጊዜ ነው የተሰራጨው፣ እዛም በአንደኛነት ምርጥ የተሸጠ መጽሐፍ ሆኗል። እናም ኃያሉ እግዚአብሔር፣ ዶክተር ዮንጊ ቾንን በሚያስደስት መንገድ እየተጠቀመባቸው ነው። ዶክተር ዮንጊ በቤተክርስቲያኑ ወደ 800,000 የሚደርሱ አባላት አሉት፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ለዚህ መጽሐፍ እየተጠቀመው ነው፣ እግዚአብሔር እሱን ለዚህ መጽሐፍ መርጦታል። አመሰግንሃለሁ ጌታዬ፣ መጽሃፉ የጌታችን የኢየሱስ የመጨረሻ ሰአት (ዘመን) መጽሐፍ ነው። ጌታችን ሁሉም ክርስቲያኖች ይህንን መጽሐፍ እንዲያነቡትና ለሌሎችም እንዲመሰክሩ ይፈልጋል፤ እናም ብዙ ሰዎች እያረጉ ያሉት ይህንኑ ነው። አንድ መጽሐፍ ሲገዙ፣ ደርዘን ይገዛሉ፣ በመቶዎች ይገዛሉ፣ እናም ይሄ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጎን ለጎን ምርጥ የመመስከሪያ መሣሪያ ነው ይላሉ። እናም በመቀጠል፣ ብዙ ኢሜል(email) ይደርሰኛል፣ ከእንግዲህ በኋላ ለራሴ ምንም ጊዜ የለኝም። እናም በተለየ መልኩ ከትንንሽ ሕፃናት ማለትም 12፣13 ዓመት ከሆናቸው ኢሜይል ይደርሰኛል። ከዚህ መጽሐፍ ጋር በጣም ፍቅር እንደያዛቸው ይናገራሉ። እነሱ ኢየሱስን ያፈቅሩታል፣ ይህንን መጽሐፍ የኢየሱስ መጽሐፍ ብለው ይጠሩታል፣ በመጽሐፉም ብዙዎቹ ተለውጠዋል። ከእነሱ መሃል አንዳንዶቹ እንዲህ ይላሉ፣ ትምሕርት ማቋረጥና የእግዚአብሔርን ሥራ መስራት አለብን ይላሉ። ትምህርት እንዳታቋርጡ እላቸዋለሁ። መማር አለባችሁ፣ እግዚአብሔር እንድትማሩ ይፈልጋል። ታውቃላችሁ፣ ያንን ነው የምነግራቸው። ግን ምንም ስሩ፣ እግዚአብሔርን መጀመሪያ አድርጉት (አስቀድሙት) እላቸዋለሁ። ለላኩልኝ ኢሜይል መልስ ስሰጣቸው በጣም ደስተኞች ናቸው። ታውቃላችሁ አይደል፣ ሺዎችና የብዙ ሺዎች ህይወት በዚህ መጽሐፍ እየተቀየረ ነው ምክንያቱም መጽሐፉ የኢየሱስ ነው። እናም ጌታዬ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ለዚህ መጽሐፍ የገባውን ቃልኪዳን አሟልቷል (ፈፅሟል)። መልካም፣ ሁሉንም ነገር እንደሚቆጣጠር ነግሮኝ ነበር። ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው፣ መልካም፣ በጣም ተጨንቄ ነበር፣ ስለ ብዙ ነገሮች፣ ታውቃላችሁ አይደል፣ ከዛም ይህን ነገረኝ* ***“ለምንድን ነው የምትጨነቂው፣ ይሄ የእኔ መጽሃፍ ነው፣ እኔ ራሴ እቆጣጠረዋለሁ (የሚያስፈልገውን አሟላለሁ)*”፣** *ሁል ጊዜ ያንን ይነግረኝ ነበር። ግን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው እየተቆጣጠረው ነበር። መጽሐፉን የሚያነብ ማንም፣ ይህ የኢየሱስ መጽሐፍ እንደሆነ ያውቃሉ እናም እርሱ(ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ) ሁሉም ነገር ላይ ቁጥጥር አድርጓል። ስለዚህ እርሱ ለዚህ መጽሐፍ የገባውን ሁሉንም ቃልኪዳኑን ፈጽሟል። አሁን የቀረ አንድ ነገር ቢኖር የእኔ የዳንስ አገልግሎት ነው። የዳንስ አገልግሎቴን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አሰልጥኖኛል፣ ይህ ቅዱስ ዳንስ ነው፣ ለሶስት አመታት፣ ከዛም ለሁለት አመታት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ደንሻለሁ። አሁን ወደ 3 ዓመታት ተኩል እየሆነው ነው፣ አሁንም ጌታን እየጠበቅሁ ነው። እግዚአብሔርን ለማገልገል መጠበቅ በጣም ከባዱ ነው። ታውቃላችሁ አይደል፣ ጌታ ኢየሱስ መጽሐፉን ከማሳተሙ በፊት 7 አመት መጠበቅ ነበረብኝ። አንዳንዴ፣ መጽሐፉን ያሳትመዋል (ሊያሳትመው ይሆን) ብዬ አስባለሁ፣ ነገር ግን እርሱ ቃሎቹን ጠብቋል፣ ኢያችሁ*።

**--------አቅራቢው እየተናገረ:---------**

በገነታዊ ጉብኝቶቿ መጨረሻ፣ ኢየሱስ ለቹ እጅግ ልዩ የሆነ ቃልኪዳን አደረገላት (ገባላት)።

**--------ቱ ቶማስ እየተናገረች:---------**

*መልካም፣ የመጨረሻው ጉብኝት የመጽሐፉን የእጅ ጽሁፍ ካጠናቀኩ በኋላ ነበር። በመቀጠልም በዚህ ምድር በሚገኘው ባህር ዳርቻ አመጣኝ። እናም ለተወሰኑ ሰአታት አብረን አሳለፍን። ሁል ጊዜ ሰኞ ሰኞ እዛ እንደሚያመጣኝ ነገረኝ። ያ ሜይ 27, 1996 ነበረ። ከዛን ቀን ጀምሮ፣ አንድም ቀን አሳልፎ አያውቅም። እሱ ሁሌ ሰኞ ሰኞ በተለወጠው አካሌ እዛ ይወስደኛል። ሁሌ ሰኞ ጠዋት ከ12 ሰዓት ጥቂት ደቂቃዎች አለፍ ብሎ ይቀሰቅሰኛል፣ እርሱ ለ30 ደቂቃዎች አካሌን ያነቃንቀዋል፣ 30 ደቂቃ ብቻ፣ ከዛ አያንስምም፣ ከዛ አይበልጥምም፣ ከዛ ይገለጥልኛል፣ ከዛ የእርሱ መንፈሳዊ አካልና የእኔ መንፈሳዊ አካል አንድ ላይ ወደ ምድራዊው የባህር ዳርቻ እንሄዳለን። ከዛ በመቀጠል እዛ ስንሄድ፣ ታውቃላችሁ አይደል፣ ብዙ ጊዜ እርሱ ያወራል፣ እኔም አዳምጣለሁ። ከዛ እኔ እዘምራለሁ፣ በመንፈሳዊ አካሌም እደንሳለሁ፣ እናም አሁን ላይ በህይወቴ ምርጡ (ልዩው) ጊዜ ይሄ ነው።*

**--------አቅራቢው እየተናገረ:---------**

ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተበት ምክንያት በዮሐንስ ወንጌል 3:16 አማካኝነት ነው - “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ አለሙን እንዲሁ ወዶአልና።”

ስለዚህ፣ ሮሜ 10:9 ላይ እንደተፃፈው “ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤”

**--------ቱ ቶማስ እየተናገረች:---------**

*መልካም፣ ብዙ ሰዎች “ከሞትክ በኋላ ማን ይጨነቃል” ሲሉ እሰማለሁ፣ ሂ ሂ ሂ ይላሉ፣  እንደዛ እያሉ፣ ታውቃላችሁ አይደል። ከዛ እንዲህ እላለሁ፣ ከሞታችሁ በኋላ ስላለው ነገር የበለጠ መጨነቅ አለባችሁ። ይሄ እየመሰከርኩ እያለሁ ነው። ከሞታችሁ፣ ሁለት ቦታ ብቻ ነው የምትሄዱት፣ ወይ ወደ ገነት ወይ ወደ ሲኦል፣ እሱም(የሚነገረው ሰው) እንዲህ ይላል፣ ኢኢኢኢህህህ፣ ከሞትኩ በኋላ ማን ይጨነቃል። ከሞቱ በኋላ ስላለው ነገር ምንም የማያውቁ መስለው ነው የሚያወሩት። እኔም “ከሞታችሁ በኋላ ስላለው ነገር የበለጠ መጨነቅ አለባችሁ” እላለሁ፣ ምክንያቱ ለምን? ብትሞቱም እንኳ፣ አካላችሁ (ስጋችሁ) ይሞታል፣ መንፈሳችሁ እና ነፍሳችሁ ግን መቼም አይሞትም። ለዛ ነው ህመምን፣ ደስታን፣ ሀሴትን፣ ሁሉንም ነገር ማስታወስ የምትችሉት፣ ልክ በህይወት እያላችሁ እንደነበረው ጊዜ። አሁንም ስለዛ ሊያምኑኝ አልቻሉም፣ አአአአአ፣ በእኔ ላይ ተናደዱ። “እየተናገርኩ ያለሁትን አንድ ቀን እንደምታስታውሱት ተስፋ አደርጋለሁ” እላቸዋለሁ። ኢየሱስን ታውቁታላችሁ? እነሱም “እግዚአብሔርን(አምላክን) አውቀዋለሁ” ይላሉ። እኔም፣ “መልካም፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር(አምላክ) ነው” እላለሁ። እርሱ አባት ነው፣ እርሱ ቅዱስ መንፈስም ነው፣ እርሱ ሁሉንም ነው።*

[ማስታወሻ:- “አብ ወልድ (ኢየሱስ) መንፈስቅዱስ” ሶስቱ አንድ እግዚአብሔር ብለን እንጠራቸዋለን፣ እንደ እግዚአብሔር ቃል አስተምህሮ። ቅድስት ቱ ከላይ የተናገረችው ይህንን ለማፋለስ (ለመቃረን) አይደለም። እግዚአብሔር አብ ራሱን የቻለ ቢሆንም (የራሱ አካል ቢኖረውም) ከኢየሱስ ጋር አንድ ነው፣ መንፈስ ቅዱስም ራሱን የቻለ ቢሆንም (የራሱ አካል ቢኖረውም) ከኢየሱስ ጋር አንድ ነው። 1 ዮሐንስ 5:7፣ ትንቢተ ኢሳያስ 9:6፣ የዮሐንስ ወንጌል 10:30]

*ኢየሱስን ካላወቃችሁ እግዚአብሔርን አላወቃችሁትም፣ ያ ደግሞ ወደ ገነት አይወስዳችሁም። አወራለሁ፣ አወራለሁ፣ አብዛኞቹ ሰዎች ግን ሊሰሙኝ አይፈልጉም። ይህንን እነግራቸዋለሁ፣ መልካም፣ አሁን ሊታምኑ አልፈለጋችሁም፣ አንድ ቀን እንደምታምኑ ተስፋ አደርጋለሁ። እናም አወራለሁ፣ አወራለሁ፣ ምንም ያህል ብጥር፣ ይድኑ ዘንድ ያዘጋጀሁላቸውን መቀበል አልፈለጉም። ምን እንደምል ታውቃላችሁ፣ “ይህን ትድኑበት ዘንድ ያዘጋጀሁላችሁን አለመቀበላችሁ ምንም አይደል፣ ግን አንድ ቀን፣ ሁሉም የእግዚአብሔር ሰዎች ወደገነት እንደተነጠቁ ታውቃላችሁ፣ ከዛም፣ አሁን እያልኳችሁ ያለሁትን ነገር ታውቃላችሁ፣ ግን እጠይቃችኋለሁ፣ ያ ጊዜ ሲመጣ፣ 666 ቁጥርን ምልክትን በጭራሽ እንዳትቀበሉ፣ ያንን ከተቀበላችሁ በሲኦል ለዘለአለም እስከዘለአለም ዘለአለም በእሳት ትነዳላችሁ። ስለዚህ እባካችሁ፣ እባካችሁ፣ እባካችሁ፣ 666 ቁጥርን በምንም አይነት መልኩ እንዳትቀበሉ። እባካችሁ ልታስታውሱ ትችላላችሁ? ” ታውቃላችሁ፣ አንዳንዶቹ እሺ ይላሉ። ይሄንን ለብዙ ብዙ ሰዎች ተናግሬያለሁ።*

*ማንም ከዚህ በፊት የድህነትን (የመዳኛን) ጸሎት ፀልዮ የማያውቅ ካለ፣ ልፀልይ እፈልጋለሁ። እባካችሁ ከኔ በመቀጠል ደግማችሁ በሉ።* ***ጌታ ኢየሱስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንክ እና ለእኔ ብለህ እንደሞትክ አምናለሁ። እባክህን ወደ ልቤ ና እናም ጌታዬና መድሃኒቴ ሁንልኝ። ኃጥያቶቼን ሁሉ ይቅር እንድትለኝ እና በከበረው ደምህ እንድታነፃኝ፣ ሁሉንም የህይወቴን ቦታ ከአሁን (ከዚህ ሰዓት) ጀምሮ እንድትቆጣጠረው እጠይቅሃለሁ። ኢየሱስ ሆይ፣ በመንፈስ ቅዱስህ ሙላኝ እናም ለክብርህ ትጠቀምብኝ ዘንድ(አገልጋይህ እሆን ዘንድ) ኃይልን አስታጥቀኝ። እኔ በህይወቴ ዘመን ሁሉ አንተን አገለግልህ፣ አፈቅርህ፣ እታዘዝህ ዘንድ እና በሌሎች ህይወትም ልዩነትን አመጣ ዘንድ እፈልጋለሁ። አባት ሆይ፣ ልጅህ ስላደረግኸኝ አመሰግንሃለሁ። በኢየሱስ ቅዱስ ስም። አሜን። ሀሌ ሉያ።*** *ማንኛችሁም ከእኔ ጋር ይህን ጸሎት የጸለያችሁ፣ እባካችሁ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂዱ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ከካህናት (ፓስተርስ) ስሙ እና መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ አንብቡ፣ ተማሩት። በየቀኑ ብዙ ጊዜ (ሠዓታት) ጸልዩ፣ ከኢየሱስ ጋርም ግንኙነት (የጠበቀ ወዳጅነት) ይኑራችሁ። አመሰግናሁ፣ አሜን፣ ሀሌ ሉያ።*

**--------አቅራቢው እየተናገረ:---------**

በ ቹ ቶማስ አገልግሎት ስም፣ ዝግጅታችንን ስለተመለከታችሁ አመሰግናለሁ። በ “ገነት በጣም እውነታ ነው” ላይ፣ “***ካሰብነው በፊት ቀደም ብሎ ለቤተ ክርስቲያኑ በድጋሜ እንደሚመጣ” ኢየሱስ ተናግሯል***፣ ስለዚህ ተዘጋጁ እናም ለአምላካችን (እግዚአብሔር) ሁሉንም ምስጋና እናቅርብ።

[የተርጓሚው መልዕክት: ማራናታ፣ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ቶሎ ና።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ ልጅ ቅዱስ እንደሆነ እናንተም በእርሱ አምናችሁ በቅድስናና በንፁህ ልቡና ኑሩ

መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ ራእይ 13 እና 14 ላይ በመጨረሻው ሰአት (ዘመን) ስለ አንድ አውሬ (የክርስቶስ ኢየሱስ ተቃዋሚ) መነሳት ይገልፃል። ለአለም ሰላም አመጣለሁ ብሎ አለምን ስለሚያስት አውሬ ስለተባለው ሀሰተኛ፣ እንዲሁም ሰዎች ለመጀመሪያው አውሬና ለምስሉ እንዲሰግዱ እንዲሁም የሰይጣንን ምልክት 666ን እንዲቀበሉ የሚያስገድድና ብዙ ታላላቅ ምልክቶችን ስለሚያሳይ በሰይጣን የሚመራ ሀሰተኛ ነብይ (ሁለተኛ አውሬ) እንደሚነሳ ተናግሯል። ስለዚህ ወንደሞች ሆይ፣ ተጠንቀቁ፣ ይህ የአውሬው ምልክት 666 ግምባር ላይ ወይም በእጅ ላይ የሚቀበር ሰይጣናዊ ምልክት ነው። በምንም አይነት መልኩ 666ን እንዳትቀበሉ፣ ማንም እንዳያስታችሁ፣ ምልክቱን የተቀበለ ማንም ለዘለአለም በእሳት ባህር እንደሚጣል እግዚአብሔር ተናግሯል። ለዘለአለም በእሳት ባህር ከመጣል፣ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብላችሁ አንገታችሁን ብትቆረጡ እጅግ እጅግ ይሻላል ፣ ጌታ አዳኝ መድሃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳለ “በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳ አስነሳዋለሁ የዘለአለም ህይወትንም እሰጠዋለሁ” ብሏል። በጸሎት ትጉ፣ ተፋቀሩ፣ የጌቶች ጌታ የነገስታት ንጉስ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመከራ ያድናችኋል፣ እንደቃሉ ኑሩ እንጂ የአለምን ከንቱ ፈቃድ አትፈፅሙ።

እባካችሁ፣ አሁን የአሜሪካን ፕሬዝዳንት የተባለውን ባራክ ሁሴን አባማን እና ሌሎችንም ተጠንቀቁ፤ አውሬው ወይም የክርስቶስ ተቃዋሚ እንደሚነሳ ሰምታችኋልና። የናዝሬቱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ 24፣ “ማንም እንዳያስታችሁ፣ በስሜ ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነን እያሉ ይመጣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ” ብሎናልና ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። አር ኤፍ አይ ዲ የተባለውን ምልክት እንዳትቀበሉ!፣ ይህ ምልክት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከተጠቀሰው የአውሬው ምልክት 666 ጋር ተቀራራቢ ነው ምክንያቱም በቀኝ እጅ ወይም በግምባር ላይ ስለሚቀበር። ስለዚህ የአውሬው ምልክት ስለሚሆን (ሊሆን) ስለሚችል ተጠንቀቁ። ክብር ለእስራኤል አምላክ ለሰራዊት ጌታ ኤልሻዳይ አዶናይ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሁን። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሠላም፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ለሆናችሁ ቅዱሳን፣ ክርስቶስ ኢየሱስን ከምትወዱና የቅዱስ አባቱን ፈቃድ ሁል ጊዜ ከምትፈፅሙ ጋር ለዘለአለም ይሁን፣ ክብር ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን፣ ሀሌ ሉያ፣ አሜን።]

Translated to Amharic by Thomas Getachew Tuta, hithomasgetachew@gmai1.com